ቀን፤ ጁላይ 31፣ 2020

**የቦርድ መረጃ፤** __X___

**የስብሰባ ዝግጅት፤** __X___

**ከ፡** ዶ/ር ቴሪ ኤች. ማዚንጎ (Terri H. Mozingo) Ed.D., Chief of Teaching, Learning, and Leadership

**በኩል ፤** ዶ/ር ግሪጎሪ ሲ .ሐትዚንግስ(Gregory C. Hutchings) Jr. የትምህርት ቤቶች ሱፐር ኢንቴንደንት

**ለ ፤** የተከበሩ Cindy Anderson፣ ሊቀመንበር እና
የአሌክሳንደሪያ ከተማ ትምህርት ቤቶች ቦርድ አባል

**ርእስ፤** የቀጣይ ትምህርት እቅድ 4.0 ፤ ትምህርት ቤቶችን በልዮ ሁኔታ ማሰብ (Reimagining Schools (PDF) ወቅታዊ መረጃ

**ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. 2020 የስትራቴጂ እቅድ ግብ**
ግብ 2፤ የትምህርት አሰጣጥ ብቃት

**የ2019-2020 ትምህርት ዓመት የትኩረት አቅጣጫ**
የትኩረት አቅጣጫ 1፤ የትምህርት ፍትሃዊነት

**2020 የበጀት ዓመት የበጀት ቅድሚያ ትኩረት**
አካዳሚ

**ማጠቃለያ**
በዚህ ሳምንት የእኛ ዘርፈ-ብዙ ስራ እቅድ አዘጋጅ ቡድኖች(CFPT) ሰኞ እና እሮብ ጥዋት ባካሄደነው የዝግጅት ስብሰባ እና ከዚያም ባሻግር የተወሳሰበ ውይይት እና የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ሲያካሂዱ የቆየውን ሂደት (Sprint 3) አጠናቆል። የእኛን ትምህርት ቤቶችን መልሶ የመክፈት ስትራቴጂ ለመደገፍ ከ150 CFPT አባላት ቢጋራ፤ በትብብር እና በተቀናጀ መልኩ ሰርተዋል። በእነዚህ ቡድኖች የተከናወነው የስራው ዋነኛ ተግባር የማስተማርና የመማር እይታ እንዲሁም ፍትሃዊነት እና በዋነኛነት የህዝብ ጤና ቅድሚያ አትኩሮት መስጠትን ይመለከታል። በዚህ ሳምንት የእኛ ስራ አትኩሮት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ነበር፤

- *የእኛ ተማሪዋች እና ሰራተኞች በእኛ ያዘጋጀውን በ100% ቨርችዋል ወይም የድብልቅ ሞዴል እንዴት ነው የሚመለከቱት?*
- *የ100% ቨርችዋል ወይም የድብልቅ ሞዴል አሁን እኛ ካለን ችግር አንፃር ሴፕቴምበር 8፣ 2020 ት/ቤቶችን መልሶ ለመክፈት ተገቢ አዋጪ ይሆናል?*

በሚቀጥለው ሳምንት ስለትምህርት ቤት መልሶ መክፈት ዝግጅት የበለጠ ዝርዝር መረጃ እና ሌሎች ጉዳዩችን ለትምህርት ቤቶች ቦርድ በኦገስት 7፣ 2020 እናቀርባለን።

**የተጠናቀቁ ተግባራት + ስኬቶች ( ጁላይ 27 - ጁላይ 31)**
***በአንድ ተማሪ፣ ሰራተኛ እና ቤተሰብ ህይወት የአንድ ቀን እንቅስቃሴ***

- ይህ እንቅስቃሴ የተካሄደው በመላው CFPTs ሰኞ፣ ጁላይ 27፣2020 ሲሆን አንድ ጉዳዮ የሚመለከተው ሰው ቀኑን በሙሉ በድብልቅ እና በቨርችዋል ሞዴል የሚያሳልፈውን ቆይታ በዝርዝር ያሳያል። ይህ ሂደት የሚያሳየው የትምህርት ቤት የጊዜ ሰሌዳ እና አቀራረፅ በአንድ ተማሪ፣ ሰራተኛ ወይም የቤተሰብ አንፃር እይታ የሚኖረውን ሁኔታ እንድንረዳ አስችሎናል።
- እኛ በእያንዳንዱ ተማሪ፣ ሰራተኛ እና ቤተሰብ የሚወሰዱ ጥቃቅን እርምጃዋችን ሁኔታ የሚመለከት እቅድ ለማዘጋጀት እና ለመቆጣጠር የማይቻል መሆኑን የምንረዳ ቢሆንም ማድረግ የምንችለው ነገር ብዙም እድል ሊያገኙ የማይችሉትን ሃሳብና አንዳንድ ሁኔታዋች ለማካተት የሚያስችል አቀራረፅ እንዲሁም በእያንዳንዱ ሰራተኛ፣ ተማሪዋች ሊያጋጥሙ የሚችሉ ፈተናዋችን ፣ ተማሪዋችን እና የኮሚዮኒቲ አባላት ለመከታተል የሚያስችል እንዲሆን መሞከር ነው።

- በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ብዙ ተሳታፊዎች በቨርችዋል እና በድብልቅ ሞዴል የትምህርት አሰጣጥ ሂደት በሚከተሉት መስኮች በርካታ ማነቆዎች እንደሚኖሩ ተመልክተዋል፤
    - በቨርችዋል ቀን ተሳታፊዎች የተማሪዎችና የሰራተኞች የአእምሮ ጤንነት እና የፊት ለፊት ግንኙነት ፣ ለሲንክሮኒክየስ ትምህርት የቨርችዋል የትምህርት አሰጣጥ ሞዴል ማካሄድ፣ የWi-Fi ግንኙነት እንዲሁም ሌሎች የቴክኒዋሎጂ ችግሮች የምግብ አገልግሎት ፣ ያልተቆረጠ የመረጃ ልውውጥ እና የልጆች ጥበቃ አገልግሎት ችግር ሊኖር እንደሚችል አመልክተዋል።
    - በድብልቅ ሞዴል የትምህርት ቀናት ተሳታፊዎች በርካታ ጥያቄዎች በጤና ምርመራ ማጣራት ስራ፣ ትምህርት ቤት ከመጀመሩ በፊት፣ በት/ቤት ቆይታ ወቅት እና ከትምህርት በኋላ፣ የሰራተኛ ውጤታማ ስራ ማከናወን፣ የተማሪ ለተማሪ ግንኙነት እና በሳምንቱ ውስጥ የትምህርት ቤት ባህል መጠበቅ።
- በዚህ ሂደት እኛ ቀጣይ የእቅድ ዝግጅት በምንሰራበት ወቅት እና ሪሶዋርሶችን ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. እና ከእኛ ኮሚዮኒቲ ጋር በምንጋረበት ወቅት የሚታዩ "ክፍተቶችን" አሳይቶል እንዲሁም የእኛ ቨርችዋል እና የድብልቅ የጊዜ ሰሌዳ የጊዜ ሰሌዳ እንድንረዳ አግዞናል። እያንዳንዱ ዘርፈ-ብዙ ስራ እቅድ አዘጋጅ ቡድኖች ይህን ልምድ በመመለከት የሚያዘጋጁትን መመሪያ እና ማቴሪያሎችን እንደሁኔታው እንዲለውጡ አድርጎል።

*የአዋጪነት ትንተና*

- የCFPT ሊቀመንበሮች በዘርፈ-ብዙ ስራ እቅድ አዘጋጅ ቡድኖች የተጠናቀቀው ማቴሪያል እና ትንተና እንዲሁም ሪሶዋርሶችን ከብሄራዊ፣ ስቴት እና የአካባቢው ኤክስፐረቶች በመታገዝ አንድ ላይ የድብልቅ እና የቨርችዋል ሞዴሎች አዋጭነት ለማጥናት ለመመልከት ችለዋል። እያንዳንዱ ሊቀመንበር ለተመሳሳይ ጥያቄዎችን ከCFPT ከተሰጠው ኋላፊነትና የስራ ድርሻ አኳያ ምላሺ ሰጥተዋል፤ *"በአካል በመገኘት ትምህርት ለመስጠት ትምህርት ቤቶችን ሴፕቴምበር 8፣ 2020 መልሶ መክፈት ተገቢ ይሆናል?"* በተለይ ዝርዝር መልኩ፤
    - አሁን ባሉት ችግሮች ማነቆ ሊሆኑ የሚችሉ ነገሮች እና ባሉት ሪሶዋርሶች ይህ ሞዴል ተግባራዊ ሊሆን ይችላል?
    - ይህ ሞዴል የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪ፣ ሰራተኞ እና ቤተሰቦችን ፍላጎትና ምርጫዎች ድጋፍ ሊይደርግ ይችላል?
    - ይህ ሞዴል ከኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. 2025 እቅድ ጋር እንዴት ይጣጣማል? *ፍትሃዊነት ለሁሉም?*
- እያንዳንዱ ሊቀመንበር ለዶ/ር ሐትቺንግስ ያቀረቡት ሃሳብ ያለውን የመገልገያ ችግር ፣ የጊዜ ሰሌዳ ፣ የትራንስፖርት፣ የግል መከላከያ መሳሪያዎች(PPE) እና የሰራተኞች ጉዳይ ችግር በመጥቀስ ትምህርት ቤቶች ሴፕቴምበር 8፣ 2020 መልሶ መክፈት ተገቢ አዋጪነት የለውም ብለዋል። ዝርዝር ትንተና በኦገስት 7፣ 2020 ለትምህርት ቤቶች ቦርድ ስብሰባ ይቅርባል።

*ምስጋና እና የወደፊት አቅጣጫ*

- ወደፊት የሚኖረውን ሁኔታ ስንመለከት ስንረዳ እንደ CFPT ቡድን እነዚህ ነገሮች እንዴት ለውጥ እያሳዩ እንደሆነ ወደኋላ መመልከት ጠቃሚ አሰራሮችን መለየት፣ አዳዲስ መጀመር እንዲሁም ሌሎች ነገሮችን ደግሞ ለማቆም መመልከት ያስፈልገናል።
- በዙም ውይይት፣ በኢሜል እና በዚህ Padlet ለመላው ቡድኑ የተገለፀውን ምስጋና ለማሳወቅ ጥቂት ጊዜ መወሰድ ተገቢ ይሆናል። በእነዚህ አስተያየቶች ግልጽ የሆነ ጉዳይ በመላው የእኛ አዘጋጅ ቡድኖች የጠለቀ ትብብር መኖር ግንኙነትን እንደሚያጠነክር፣ ክብር እንደሚገነባ እና ዝግጅትና እንደሚያሰፋ ታውቆል።

**ቀጣይ ተግባራት ( ኦገስት 3 - ኦገስት 7)**

- ዘርፈ-ብዙ ስራ እቅድ አዘጋጅ ቡድኖች እንዲሁም ሊቀመንበሮች እና ከፍተኛ የአመራር አባላት ቡድን ለውጪው ወገን ለማሳወቅ የሚያስችል ስራቸውን አጠናቀዋል የእኛን የአዋጪነት ትንተና ጥናት ጭምሮ ፣ የርእሰ መምህራን መልሶ መክፈት አሰራር መመሪያዎች እና ወርክቡክ የተደረጉት ውይይቶች እና በጁላይ 2020 በእያንዳንዱ ቡድን የተፈጠሩ ትብብሮች የሚያሳይ ።
- ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በፎል ወቅት 100% ቨርችዋል ፕለስ ትምህርት ቤት መክፈት ሞዴል በስራ ለማዋል እና ከፍተኛ ጥራት ያለው አገልግሎት ለእኛ ተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና ቤተሰቦች ለመስጠት እነርሱ ባሉበት ደረጃ ከእነርሱ ጋር መገናኘት ይኖርብናል እና ከእኛ ተማሪዎች ጋር መስራት ይኖርብናል። የዚህ ዋና አካል የሆነው ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ተማሪዎችን፣ እና ሰራተኞች ለማገዝ በዚህ ለሁሉም አዲስ ልምድ በሆነበት ሁኔታ ማድረግ የሚችለውን ሁሉንም ማድረጉን ማረጋገጥ ነው። ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. በጣም ወሳኝ በሆኑ መስኮች እንዴት በጥሩ ሁኔታ ድጋፍ መስጠት እንደሚችል ከተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና ሰራተኞች በቀጥታ የተሰጠው አስተያየት እና ሃሳብ የእቅድ ሂደቱን በማሻሻል እና ተፈላጊ ትብብር በመፍጠር ውጤታማ የሆነ ትምህርት ቤት መልሶ የመክፈት እንቅስቃሴ እገዛ ያደርጋል። ወሳኝ የሆኑ የድጋፍ መስኮች የተለዩት ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር በጁላይ ወር በመጠይቅ በማሰራጨት እና በኮሚዮኒቲ ውይይቶች በፎል ወቅት ሊኖር ስለሚችሉ ፍላጎቶች ለመረዳት የተሰባሰበ መረጃ ነው።
- ለረቂቅ እቅድ ሃሳቡ በኦገስት 7፣ 2020 ለማቅረብ የተደረጉ ዝግጅቶች እና የድጋፍ ማቴሪያሎች የተማሪዎችን የሰራተኞና ቤተሰቦች እና የኮሚዮኒቲ አባላት ሪሶዋርስ።

*ቀጣዮ የእኛ  የጊዜ ሰሌዳ (timeline) የሚከተሉትን ወሳኝ ከንውኖች ያካትታል።*

- አጠቃላይ እቅድ ከዝርዝር መረጃዋች ጋር በትምህርት ቤት ቦርዱ አርብ ፣ ኦገስት 7፣ 2020 ቀርቦ ውይይት ይደረጋል።
- ከትምህርት ቤት ቦርዱ በስብሰባው የቀረቡ ሃሳቦችን ያካተተ የተሻሻለ እቅድ ከዝርዝር መረጃ ጋር ለኮሚዮኒቲው እሮብ ኦገስት 12፣ 2020 ይገለፃል።
- የመጨረሻው እቅድ ለቨርጂኒያ ትምህርት ዲፖርትሜንት አርብ፣ ኦገስት 14፣ 2020 ተዘጋጅቶ ይቀርባል።

**ቅድመ መነሻ ሁኔታዋች (ባክግራውንድ)**

በኮቪድ COVID-19 ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርት ቤቶች ከተዘጉ ጀምሮ የአሌክሳንደሪያ ከተማ የሕዝብ ት/ቤቶች (ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ.) ለተማሪዋች እና ቤተሰቦች የተለያዮ የትምህርት እድሎችን ማቅረቡን ቀጥሎል።  የእኛ የትምህርት አስተደደር ዲቪዝን በዚህ ችግር ወቅት ለተማሪዋች እና ቤተሰቦች የቴክኖሎጂ አቅርቦት በማመቻቸት ፣ የመማሪያ ማቴሪያሎች በማቅረብ፣ የትምህርት ቁሶቁሶች፣ ምግብ እና የአገልግሎት ድጋፍ አድርጎል ።  እንደሚያውቁት ትምህርት ቤቶች ከተዘጉ ጀምሮ የእኛ የተጠናከረ ቀጣይ ትምህርት እቅድ 4.0 የተማሪዋችን፣ ሰራተኞች ፍላጎቶች ላማሞላት ሞክሮል። የተጠናከረ የቀጣይ ትምህርት እቅድ 2.0  የትምህርት ሪሶዋርስ እንዲሰፋፋ አግዞል፤ የተማሪዋች የተዘጋጀ የትምህርት ማቴሪያሎችን  ፣ የሲንክሮኒከየስ ትምህርት፣ አሲንክሮኒከየስ ትምህርት  እና የኦንላይን ትምህርት በማዘጋጀት፣ የቀጣይ ትምህርት እቅድ 3.0 የበጋ ትምህርት ተሳትፎን በማጠናከር እና የተሳትፎ እና የማጠናከሪያ በጋ ትምህርት ለሁሉም እቅድ የትምህርት እውቀት መርሳት፣ ተሳትፎና ማጠናከሪያ እንዲሁም የቀጣይ ትምህርት እቅድ 4.0  ትምህርት ቤቶችን በልዮ ሁኔታ ማሰብ የእኛ ትምህርት ቤቶን መልሶ መከፈት ሂደት አቅጣጫ ያሲዛል።

የኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. የተሻሻለ ቀጣይ ትምህርት እቅድ 4.0 ዝግጅት፤ ትምህርት ቤቶችን በልዮ ሁኔታ ማሰብ ት/ቤቶች መልሶ የመክፈት አሰራር በፌደራል፣ ስቴት እና ከአካባቢው መመሪያዋች ጋር እንዲጣጣም ተደርጎል። የመጨረሻው እቅድ በመጨረሻም ለተማሪዋች፣ ለሰራተኞች እና ለቤተሰቦች ጤናማ እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢ ሁኔታ መፍጠርን ያረጋግጣል። ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. ትምህርት ቤቶች መልሶ ለመክፈት በመስራት ላይ ይገኛል። እኛ አስተያየት ከመሪዋች፣ ከአስተማሪዋች፣ ሰራተኞች፣ ተማሪዋች ፣ ቤተሰቦች እና ኮሚዮኒቲ አባላት ማሰባሰብ ይኖርብናል። ስለሆነም ውጤታማ የሚሆኑ እና መልሶ ለመከፈት የሚስፈልጉ ነገሮችን የሚያካተት ጥሩ እና ተግባራዊ ሊሆን የሚችሉ ሃሳቦችን ማሳባሰብ ይኖርብናል። በመጨረሻም እቅዱ ትምህርት ቤቶችን መልሶ ለመክፈት የሚኖረውን እቅድ አዋጪነት ይመለከታል።

**የመፍትሄ ሃሳብ**

ሱፐር ኢንቴንደንት አርብ፣  7፣ 2020 ለሚካሄደው ስብሰባ ለመዘጋጀት የትምህርት ቤት ቦርዱ በዚህ የቀረበውን  የመፍትሄ ሃሳብ መረጃ እንዲያጠኑ ጠይቅዋል።

**አባሪ ሰነዶች**

1. አንድ ቀን ቆይታ እንቅስቃሴ ናሙና ምሳሌ - ተማሪ I
2. አንድ ቀን ቆይታ እንቅስቃሴ ናሙና ምሳሌ - ተማሪ II
3. አንድ ቀን ቆይታ እንቅስቃሴ ናሙና ምሳሌ - አስተማሪ 1
4. የአዋጪነት ትንተና ናሙና
5. የዘርፈ-ብዙ ስራ እቅድ አዘጋጅ ቡድኖች መግለጫ ፓወር ፓይንት (በጃላይ 29፣ 2020 የቀረበ)

**የሚኖረው ተፅእኖ፤**

ኤ.ሲ.ፒ.ኤስ. አጠቃላይ  የመልሶ መከፈት እቅድ በማዘጋጀት በስራ እንዲውል ሁሉም ተማሪዋችና ሰራተኞች ጤናማ፣ ደህንነት የተጠበቀ እና በመልሶ መከፈት ተሳትፎ የሚያደርጉበት ሂደት መኖሩን ማረጋገጥ የCDC የቀረቡ መስፈርቶችና አሰራሮችን ጭምር መከተልን ይጨምራል።  የመልሶ መከፈት እቅድ እንደሚያረጋግጠው ተማሪዋች ከግል ሁኔታ ጋር የሚጣጣም የአካዳሚ ድጋፎች እና የጣልቃ መግባት ድጋፎችን ያገኛሉ በትምህርት ቤት መዘጋት ምክንያት የሚያጋጥሙ የትምህርት መርሳት ችግሮችን ለመቀነስ።

**ለመገናኛት**

ዶ/ር ቴሪ ኤች. ማዚንጎ (Terri H. Mozingo) terri.mozingo@acps.k12.va.us